# ውዳሴ፡ማርያም።

## ቅዱስ ኤፍሬም የደረሰው ።

ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ
የመጣው ንባቡና ትርጓሜው ።
የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደ ጻፉትና
እንደ ተረጐሙት ።

በኢትዮጵያ መንግሥት፣ አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ማተሚያ ቤት ታተመ ።
በ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረት ።

www.ethiopianorthodox.org

ውዳሴሃ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲ ተ አምላክ ዘይትነበብ በዕለተ ሠኑይ።

ይኸነን መጽሐፍ ኤፍሬም ሶርያዊ ኤፍሬም ለብሐዊ ተናግሮታል። ሶርያዊ በሀገሩ ለብሐዊ በተግባሩ ያሰኛል። ይህም ቅዱስ ኤፍሬም የያዕቆብ ዘንጽቢን ደቀ መዝሙር ነው። ያዕቆብ ዘንጽቢንም ቀጥሮ ከ፫፻፲፰ት ነው ለአውግዞተ አርዮስ ሲሄድ አስከትሎት ሂዶ ነበር። አርዮስን አውግዘው ሃይማኖት መልሰው ተመልሰው ካደሩበት ቦታ ዓምደ ብርሃን ከምድር እስከ ሰማይ ተተክሎ ሌሊት በሕልሙ ራዕይ ያያል። ራዕዩን እንደ ገለጽክልኝ ባለቤቱንም ግለጥልኝ ብሎ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት የታዘዘ መልአክ ወጥቶ ባስልዮስ ዘቂሳርያ ነው። ለቤተ ክርስቲያን ዓምድ ጽንዕ ነውና በትምርቱ የሰውን ልቡና ብሩህ ያደርጋልና እንዲህ ባለ አርአያ አየኸው አለው። ባስልዮስም ቀጥሮ ከሠለስቱ ምዕት ነው ደርሶም ተመልሶም እንደሆነ በደዌም በእርግናም ምክንያት ቀርቶ እንደሆን አልታወቀም። ከዚህ በኋላ መምሕርን ከወጡበት ሳያገቡ ትቶ መሄድ ፈሊጥ አይደለምና መምሕሩን ከወጣበት አግብቶ ስለሶስት ነገር ይሄዳል መጀመሪያ እንዲህ ካለ ሰው ጋራ ቢጫወቱ መንፈሳዊ ነገር ይገኛልና ብ

www.ethiopianorthodox.org

ው በሉ ትንቢቱ ምሳሌው ሊፈጸም ። ትንቢት ናሁ
ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ተብሎ ተነግሯል
ምሳሌውም ከኀቱም ምድር አዳም ተገኝቷል ጌታ
ም በኀቱም ማኅፀን ለመወለዱ ምሳሌ ። ሔዋን ከሕ
ቱም ገቦ ተገኝታለች ጌታም በኀቱም ማኅፀን ለ
መወለዱ ምሳሌ።ቤዛ ይስሐቅ በግዕ ከኀቱም ጉንድ ተ
ገኝቷል ቤዛ ዓለም ክርስቶስ በኀቱም ማኅፀን ለመወ
ለዱ ምሳሌ ። ጽምአ እስራኤልን ያበረደ ውሀ ከኀ
ቱም ዕብን ተገኝቷል ጽምአ ነፍሳትን ያበረደ ማየ
ሕይወት ጌታ በኀቱም ማኅፀን ለመገኘቱ ምሳሌ፤
ጽምዓ ሶምሶንን ያበረደ ውሀ ከኀቱም መንሠከ አ
ድግ ተገኝቷል ጽምዓ ኃጥአንን ያበረደ ማየ ሕይ
ወት ጌታ በኀቱም ማኅፀን ለመገኘቱ ምሳሌ ። ትን
ቢቱን ዓውቆ አናግሯል ምሳሌውንም እንጂ ዓውቆ
አስመስሏል ። ፍጻሜው እንደ ምን ነው በሉ ። ከ
መ ትኩን መራኂተ ለሃይማኖት ዓበይ እንጂ ይላ
ቃል ስትወልደው ማህተመ ድንግልናዋ እንዳልተለ
ወጠ ሰው ሲሆን አምላክነቱ ላለመለወጡ ። ድንግ
ል ወእም ስትባል መኖሯ አምላክ ወሰብእ ሲባል
ለመኖሩ ምሳሌ ነውና ።

ለሔዋን እንተ አስሐታ ከይሲ ።

ከይሲ ባሳታት በሔዋን።ምነው ከይሲ ሓለ ዲያብሎ
ስ አይደለም ያሳታት ቢሉ በልሳነ ከይሲ ተሠውሮ
ነውና ፤ አንድም በማኅደሩ ከይሲ አለው ኃዳሪን በ
ማኅደር ማኅደርን በኃዳሪ መጥራት ልማድ ነውና፤

www.ethiopianorthodox.org

ልትቀዳ ሄዳ ። ውሀ ቀድታ ስትመለስ የተጸማ ከል
ብ አገኘች በጫማዋ ቀድታ አጠጥታዋለች ። እንዱ
ም ርኅርኅተ ልብ የሚያሰኛት ይህ ነው። እህቱ ይህ
ን ያህል ርኅራኄ በዚህ ወራት እምላክ ከድንግል ይ
ወለዳል ይባላል ከንቺ ይሆን አሏት ። ወዲያው መ
ልአኩ መጥቶ ትፀንሲ አላት ። ዝም ብላ ሄደች ። ከቤ
ትም ደርሳ ውሀውን ስታወርድ ትፀንሲ አላት ። ይህ
ነገር ደጋገመኝ ከቤተ መቅደስ ሂጄ ልረዳው ብላ
ከደናግለ እስራኤል ጋራ ተከፍላ እያሰማማች የም
ትፈትለው ሐርና ወርቅ ነበር ያን ይዛ ሄደች።ከቤተ
መቅደስ ተቀምጣ ሐርና ወርቁን እያሰማማች ስትፈት
ል።መልአክ መጥቶ ትፀንሲ አላት ። እፎኑ ይከውነኒ
ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ አለችው እመቤታችን
ም ይኽን ማለቷ ስታው አይደለም ዘንተ ትቤ ድንግ
ል በእንተ ዘኢዓርገ ውስተ ልባ ሀሊና እንለ እመሕ
ያው እንዲል።እኔ ይህን አላደርገውም እንደምን ይ
ሆናል ስትለው ነው።ከዚህ በኋላ መንፈስ እግዚአብ
ሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ አላት ይኩነኒ በከመ ት
ቤለኒ አለችው።ይህን ቃሏን ምክንያት አድርጎ ። ቃ
ለ እግዚአብሔር በአፃብዓ መንፈሳ ቅዱስ በማኅፀ
ኑዋ ተቀርፁዋል ።

ጸሎታ ወበረከታ ወምሕረተ ፍቁር ወልዳ
የሃሉ ምስለ ፍቁራ ኃይለ ሥላሴ ተፈሪ መኰንን ።

www.ethiopianorthodox.org